# ተቆጩና——————————ተቆጡ፤

ለምን አትቆጩም?——————መዝናችሁ አትቆጡም?
ግፍ ሲደርስበት ወገናችሁ፤
ስትበደል በአደባባይ እህታችሁ?
የታለ ወንድምነታችሁ???!
አለሁ ባይነታችሁ?
መቼ ነው የምትቆጩት? የምትቆጡት?
ወይ ነዶ!! የምትሉት?
የሚሰማችሁ እውነተኛ ኢ–ት–ዮ–ጵ–ያ–ዊ–ነ–ት?
የወገን መብት መደፈር እንዲርቅ፤
እንዲቀር መናቅ፤
መኖር ያለመሳቀቅ፤
እንዲሠፍን።
እናንተ አትዮጵያውያን፤
ለምን አትቆጩም? ካስፈለገም አትቆጡም?
በዓይናችሁ እያያችሁ?
በጆሮአችሁ እየሰማችሁ?
እስከ መቼ ነው ዝም!?
ል——ጉ————ም?
ቁጭ————ፍጥጥ
ዐይን ቅልውጥ፤
ከንፈር ምጥጥ?
አባካችሁ በኅብረት ተቆጩና፤——————ተቆጡ፤
በጨለማም ቢሆን አፍጡ፤
ሲነጋ ድርጁ፤
የታጠቀ ዝግጁ፤
እ————ን————ድ————ት——ሆ——ኑ።
አትንኩን በሉ ግድ የለም።
ሞት እኮ አይቀሬ ነው።
ስም ነው፤
ሥራ ነው፤
ከመቃብር በላይ የሚቀየው፤
እናንተ አትዮጵያውያን ወንድሞች፤
አባቶች፤ እናቶች፤ እህቶች፤
የፍትሕ ያለህ ማለትን ልመዱ፤
ድምጽ ለሌለው ለተጎዳ መጮኽ ውደዱ፤
ሰለአንድ ወገናችሁ መብት ሠልፍ ውጡ ንጎዱ፤
ኀበዝ!!! በድረ ገጽ ላይ ስላየነው?
በጋዜጣ ተጽፎ፤
በራዲዮ ተለፍፎ፤————ስለሰማነው፤
መብት ረገጣው ሩቅ መስሎን ይሆን?
በዝምታ የተቀበልነው?



EthioLion.Com

ዕጣ ፈንታችን ያደረግነው?
አይደለም ጎበዝ በቃ ንቁ።
በኅብረት ተቆጩ፤ ከዚያም ተቆጡ፤
እንደንብ መንጋ አትንኩን ብላች አፏጩ!
ቢነኳችሁ ተናደፉ፤
በዝምታ አትለፉ፤
የአንዲት ዜጋ መገፋት፤
የአንድ ዜጋ አለአግባብ ሞት፤
**<u>የሀገር ሞት ነው፤</u>**
ቁስሉና ጠባሳው፤
ለትውልድ የሚተላለፍ፤ የሀገር ክብር አሽክላ ነው!!!
እናም በኅብረት እንቆጣ፤
የተሻለ ቀን እስኪመጣ።
ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነቱ ይከበር፤
በብቸኝነት መብቱ ተደፍሮ አንገቱን እንዳይሰብር፤
በዜግነቱ እንዳያፍር!!!

ወስብሃት ለአምላከ አበዊነ፤
በመጋቢት ወር ፳፻፬ ዓም ተጻፈ።
ሀረገወይን ስለሺ።

EthioLion.Com